የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፳፩
አዲስ አበባ — ሚያዚያ ፲፯ ቀን ፲፱፻፹፰

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

2nd Year No. 21
ADDIS ABABA – 25th April, 1996

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፴፫/፲፱፻፹፰ ዓ.ም.
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሕግ አወጣጥ ሥነ ሥርዓት (ማሻሻያ) አዋጅ ................................................ ገጽ ፻፷፱

CONTENTS

Proclamation No. 33/1996
House of Peoples'Representatives Legislative Procedure (Amendment) Proclamation .............. Page 169

## አዋጅ ቁጥር ፴፫/፲፱፻፹፰

## የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሕግ አወጣጥ ሥነ ሥርዓት አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሕግ አወጣጥ ሥነ ሥርዓት አዋጅን ማሻሻል በማስፈለጉ ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፱ (፪) እና ፶፭ (፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሕግ አወጣጥ ሥነ ሥርዓት (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፴፫/፲፱፻፹፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· ማሻሻያ

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሕግ አወጣጥ ሥነ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር ፲፬/፲፱፻፹፯ እንደሚከተለው ተሻሽሏል ፤

፩· በአንቀጽ ፪ ስር የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፭) ተጨምሯል ፤
"፭/ "የቴክኒክ እርምት" ማለት የቋንቋና የሌላም ዓይነት ግድፈት ማስተካከያ ሲሆን በማናቸውም ረገድ የሕጉን ይዘት የማይለውጥ ማሻሻያ ነው።"

፪· በአንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ (፪) መጨረሻ ላይ "ሆኖም ሕጉ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከመውጣቱ በፊት የቴክኒክ እርምት ማድረግ የሚያስፈልግ ሆኖ ሲገኝ ጉዳዩ ለምክር ቤቱ ቀርቦ እርምቱ ይደረጋል" የሚል ሐረግ ተጨምሯል።

ያንዱ ዋጋ
Unit Price } 2·30

## PROCLAMATION NO. 33/1996

## A PROCLAMATION TO AMEND THE HOUSE OF PEOPLES' REPRESENTATIVES LEGISLATIVE PROCEDURE PROCLAMATION

WHEREAS, it has become necessary to amend the House of Peoples' Representatives Legislative Procedure Proclamation;

NOW, THEREFORE, in accordance with Articles 59 (2) and 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "House of Peoples' Representatives Legislative Procedure (Amendment) Proclamation No. 33/1996."

2. *Amendment*

The House of Peoples' Representatives Legislative Procedure Proclamation No. 14/1995 is hereby amended as follows:

1) The following new sub-Article (5) is added in Article 2:
"(5) "Technical Correction" means rectification of errors of language or otherwise which in no way modifies the substance of the given law."

2) A proviso that reads, "However, where deemed necessary to make a technical correction, prior to publication of a law in the Federal Negarit Gazeta, it shall be effected by having the matter submitted to the House", is added at the end of sub-Article (2) of Article 8.

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፫· ከአንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ (፪) ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፬) ተጨምረዋል ፤

ሀ) "፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የቴክኒክ እርምት ሲደረግ ፕሬዚዳንቱ በአፈ ጉባኤው አማካኝነት እንዲያውቁት ይደረጋል ።"

ለ) "፬/ ፕሬዚዳንቱ ተቃውሞ ያላቸው እንደሆነ የተደረገው የቴክኒክ እርምት ቀርቶ በጉዳዩ ላይ የሕግ ረቂቅ ለምክር ቤቱ ይቀርባል ።"

፬· የአንቀጽ ፰ የቀድሞው ንዑስ አንቀጽ (፫) ንዑስ አንቀጽ (፭) ሆኖ ይነበባል ።

፫· <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከሚያዚያ ፲፯ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ሚያዚያ ፲፯ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ.ም.

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

3) The following new sub-Articles (3) and (4) are added after sub-Article (2) of Article 8:

(a) "3/ upon the making of a technical correction pursuant to sub-Article (2) of this Article, the President shall be notified of same through the Speaker."

(b) "4/ where the President objects thereto, the technical correction shall be dropped and a draft legislation shall be submitted to the House on the matter."

4) The previous sub–Article (3) of Article 8 is renumbered as sub–Article (5).

3. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 25th day of April, 1996.

Done at Addis Ababa, this 25th day of April, 1996.

NEGASO GIDADA (DR.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE